# የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አሰተዳደር ለመንደንገግ የተዘጋጀውን ረቂቅ አዋጅ ማብራሪያ

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ በመሸጋገር ሂደት ላይ በመሆንዋ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ወይም ከውጪ ሀገር የሚገቡ የተለያዩ ኬሚካሎች መጠን እያደገ ይገኛል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የማምረቻ እና የአገልግሎት መስጫ ተቋሞች ለግብዓትነት የሚጠቀሟቸውን ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ ከማስገባት፣ በአገር ውስጥ ከማሰራጨት፤ ከማከማቸት፣ ከማጓጓዝ ወይም በጥቅም ላይ ከማዋል አኳያ በሰው፣ በእንስሳት ጤናና በአካባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ ህጋዊ የአሠራር ሥርዓት ሊኖር ይገባል፡፡ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስገቡ እና ለሚያመረቱ ግለሰቦች ተገቢውን ብቃት ያሚሉ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት የብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት አለመዘርጋት፣ የተደራጀ ሀገራዊ የኬሚካል መረጃ አለመኖር፣ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን አስመልክቶ የክትትል ቁጥጥር ስርዓት አለመኖር በዋናነትም የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡበት ወቅት የፊዚካል ምርመራ ማለትም ከአስመጪው ድርጅት እንዲገባ የታዘዘው የኬሚካል ስም ወይም ኮድ እና በኮንቴነሩ ላይ የተለጠፈው መመሳሰሉን በማስተያየት ብቻ እንዲገባ መደረጉ ዋና ዋና የችግሩ መንስዔዎች መሆናቸውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባስጠናው ጥናት መለየት ተችሏል ፡፡

በአጠቃላይም የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በተገቢው ሁኔታ ለማስተዳደር የሚያስችል ስርዓት የሌለ ስለሆነ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮችን ለመፍታት የሚያሥችል የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡

## 2. የአዋጁ ዓላማ

የአዋጁ ዓላማ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለመመዝገብና ለማስተዳደር የሚያስችል ሀገራዊ ሥርዓት በመዘረጋት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ከማስገባት፣ ከማጓጓዝ፣ ከማከማቸት፣ ከማምረትና ከመጠቀም ሂደት ጋር በተየያዘ በሰው እና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን መከላከልና መቆጣጠር ነው፡፡ በተጨማሪም አዋጁ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

- የሀገሪቱን የኬሚካል መረጃ መሠብሠብና ማደራጀት፤
- የግልፀኝነትና የተጠያቂነት አሰራር በመዘርጋት ኬሚካሎች ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ ማድረግ ፤
- ለረዥም ጊዜ ከመከማቸት የተነሳ እና በአያያዝ ጉድለት የሚበላሹ ኬሚካሎችን በአደገኛ ኬሚካሎች አወጋገድ ስርዓት መሰረት እንዲወገዱ ማስቻል እና
- ኢትዮጵያ ከኬሚካል አስተዳደር በተገናኘ አባል የሆነችባቸውን አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶችን በብሔራዊ ደረጃ መተግበር ነው፡፡

## 3. የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር ስርዓትን የመደንገግ አስፈላጊነት

ኬሚካሎች በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ገና በማደግ ላይ ቢሆንም አሁን ያለው የኬሚካል አገባብ፣ አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ ከጤና እና አካባቢ አንፃር ሲታይ በጣም ደካማ እና መሻሻል ያለበት መሆኑ ይታመናል፡፡

በአብዛኛው ኬሚካል ወደ ሃገር ሲገባ ያለው አሰራር የብቃት ማረጋገጫ ሳይሰጥበት ቢሆንም የተወሰኑ መንግስታዊ ተቆጣጣሪ ተቋማት ለተወሰኑ አገልግሎት በሚውሉ ኬሚካሎች ላይ የተሻለ ተሞክሮ አላቸው፡፡ የእነዚህም ተቋማት አሰራር እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

1. ግብርናን በሚመለከት የሚገቡ ፀረ-ነፍሳት፣ፀረ አረም እና ሌሎች ተያያዥ የግብርና ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር በህግ ሀላፊነት የተሰጠው የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር ነው ፡፡ ሚኒስቴር መስሪያቤቱም የግብርና ኬሚካሎችን ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባት ለአስመጭዎች ፍቃድ ይሰጣል፣ ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ኬሚካሎች ዝርዝር ለይቶ ይመዘግባል ፡፡
2. የኢትዮጵያ የምግብና የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደር እና ቁጥጥር ባለስልጣን የመድሃኒት፣ ምግብና ምግብ ነክ ኬሚካሎች እና የህክምና መሳሪያዎችን ለመመዝገብ እና ለማስተዳደር የሚያስችል ስርዓት ዘርግቷል፡፡
3. የኬሚካል ጦር መሳሪያዎችን በተመለከተ የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የ OPCW (Organization for the Prohibition of Chemical Weapons) ዝርዝርን መሰረት በማድረግ የማረጋገጥ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡
4. በተጨማሪም የኢትዮጵያ የጨረር መከላከያ ባለስልጣን ጨረራ አመንጪ ኬሚካሎችን እና ቁሶችን በሚመለከት ለማስተዳደር እና ለመቆጣጠር በህግ ስልጣን የተሰጠው ሌላኛው ተቆጣጣሪ አካል ነው፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ውጪ ያሉ ኬሚካሎችን በተመለከተ ሀላፊነት የተሠጠው አካል ባለመኖሩ ኬሚካሎችን ከማምረት፣ ከማስገባት እስከ ማስወገድ ባለው ሂደት ተገቢ ባልሆነ አያያዝ ምክንያት በሰውና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ደህንነት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ለመከላከልና ለመቆጣጠር አሰቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ለማስተዳደር ለመቆጣጠር የሚያሥችል የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

አዋጁን ለማዘጋጀት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አለም አቀፍ እና ብሄራዊ ህጎች በመነሻነት ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡

- የፀረ- ተባይ ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 674/2002
- የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደደርና ቁጥጥር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 299/2006
- የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001

- Draft Chemicals Law for Protection the Environment By UNEP 2013
- The Industrial and Consumer Chemicals (Management and Control) Act, 2003 of Tanzania
- Industrial Chemicals (Notification and Assessment) Act 1998 of Australia
- Toxic Substances Control Act US EPA (TSCA Act )
- Rotterdam Convention on the Prior Informed Consent Procedure for Certain Hazardous Chemical and Pesticides in International Trade 2004

## 4. በረቂቅ አዋጁ የተካተቱ ድንጋጌዎች ይዘት

### 4.1 አጠቃላይ

ረቂቅ አዋጁ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣የብቃት ማረጋገጫ እና የኬሚካል ምዝገባ፣ መረጃ አያያዝ እና የሪፖርት አቀራረብ፣ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማሸግ፣መለያ መስጠት፣ማጓጓዝና ማከማቸትን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡

### 4.2 የአዋጁ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

በረቂቅ አዋጁ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ላይ በአዋጁ ውስጥ ትርጉም ለሚያስፈልጋቸው ቃላቶች ትርጓሜ ተሰጥቷል፡፡ በዚሁም ክፍል አንቀፅ 3 የአዋጁ ተፈጻሚነት በሚመለከት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በሚያመርት፣ ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገባ፣ ወደ ውጭ ሀገር በሚልክ፣ በሚያጓጉዝ፣ በሚያከማች፣ በሚያከፋፍል፣ በሚሸጥና በሚጠቀም ላይ ተፈፃሚ የሚሆን መሆኑን ይደነግጋል፡፡ በዚህ አንቀፅ መሰረት አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው አካላት እና ጉዳዮች እንደየአስፈላጊነቱ በአዋጁ በተካተቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች በግልፅ ተለይተዋል፡፡ በተጨማሪም የዚህ ክፍል አንቀፅ 4 የአዋጁን አላማዎች የሚደነግግ ሲሆን በዚህም መሰረት አዋጁ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለማስተዳደር እና ለመመዝገበ የሚያስችል ስርዓት በመዘርጋት ከኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንቅስቃሴ ጋር በተያየዘ በሰውና በእንስሳት ጤና እና በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጠንቆችን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችል መሆኑን ይደነግጋል፡፡

### 4.3 የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ስለ መመዝገብ

በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 5 በኢንዱስትሪ ኬሚካል እንቅስቃሴ ለመሰማራት የሚፈልግ አካል በቅድሚያ የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት እንዳለበት ደንግጓል፡፡

የአንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለተገቢው ዓላማ እንዲውሉና ከኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንቅስቃሴ ጋር በተያየዘ ሊከሰቱ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል እና ለመቀነስ ሀጋራት የተለያዩ ስርዓቶችን ዘርግተዋል፡፡ አብዛኛው ያደጉ ሀጋራት በሀገር ውስጥ በሚመረቱ እና ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ኬሚካሎች ላይ ከፍተኛ የቁጥጥር እና ፍተሻ ለማከናወን የሚያሥችል ስርዓት ዘርግተዋል፡፡ እንደ አውስትራሊያ፣ አሜሪካ እና ኤውሮፓ ህብረት ያሉ ሀገሮች አዲስ ኬሚካሎች ወደ ሀገራቸው

ከመግባታቸው በፊት የጤና እና የአካባቢ ጠንቅ ግምገማ በማድረግ ኬሚካሉ እንዲገባ ለመፍቀድ ወይም ለመከልከል የሚችሉበት ስርዓት ዘርግተዋል፡፡

በሌላ በኩል እንደ ታንዛኒያ እና ኬንያ ያሉ ታዳጊ ሀገሮች ኬሚካል እና የኬሚካል ውጤቶችን ለመመዝገብ እና ለማስተዳደር የሚያሥችል የህግ ስርዓት አዘጋጅተዋል፡፡ በመሆኑም በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 5 እና 6 በሀገራችንም የኢንዱስትሪ ኬሚካልን በተገቢው ሁኔታ ለመያዝ እና የኬሚካል መረጃን ለማደራጀት የሚያግዙ ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡

## 4.4 መረጃን አያያዝ እና ሪፖርት አቀራረብ

የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 7 እና 8 ኢንዱስትሪ ኬሚካል በተመለከተ መያዝ ያለባቸውን መረጃዎች ዝርዝር እና የመረጃዎችን ሪፖርት አደራረግን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡ ይህም የሀገራችንን የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን መረጃ በማደረጃት አካባቢ እና ጤና በተመለከተ ለሚደረጉ የፖሊስ እና ህግ ማዕቀፍ ዝግጅቶች ግብዓት የሚሆን መረጃ ከማመንጨት ባሻገር የጎላ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፋይዳዎች ይኖሩታል፡፡

## 4.5 የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማሸግ፣ መለያ መስጠት፣ ማጓጓዝ እና ማከማቸት

በዚህ ረቂቅ አዋጅ አንቀጽ 9 ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከአንድ ዓመት ስድስት ወር በላይ ሊኖራቸው እንደሚገባ የሚደነግግ ሲሆን ይህም ኬሚካሎች ለታለመላቸው ዓላማ እንዲውሉ ለማስቻል እና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከማለፉ የተነሳ የሚወገዱትን ኬሚካሎችን መጠን በመቀነስ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ኬሚካሎች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከማብቃት ጋር በተያያዘ ሊከሰቱ የሚችሉትን የጤና እና አካባቢያዊ ጠንቆችን ለመከላከል እና ለመቀነስ ያግዛል፡፡

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ተገቢውን መለያ የተደረገባቸው እና በተገቢው ደረጃ የታሸጉ መሆናቸውን ከማረጋገጥ አኳያ በረቂቅ አዋጅ አንቀጽ 10 ላይ ተገልፃል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የኢንስትሪ ኬሚካሎች መያዥያዎች አደጋ በማያደርሱ ሁኔታ እና ለማከማቸት፣ለአያያዝ እንዲሁም ጥቅም ላይ ለማዋል ምቹ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የመለያ ምልክት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው እና በመያዥያዎቻቸው ላይ ሊለጠፉ የሚገባቸውን መረጃዎች ዝርዝር በአዋጁ ተካቷል፡፡

በረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 11 እና 12 የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ከማጓጓዝ እና ከማከማቸት አኳያ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ጥንቃቄዎችን እና መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎችን ይደነግጋል፡፡

## 5. <u>ከባለድርሻ አካላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች</u>

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ለማዘጋጀት የባለድርሻ አካላት ቀጥተኛ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ከአዋጁ ዝግጅት ሂደት ጀምሮ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ረቂቅ አዋጁ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ቀጥተኛ ተሳትፎ ታይቶና ተገምግሞ በሚሰጡት አስተያየት መሰረት ማዳበር ያለበት ስለሆነ ከ20 በላይ መስሪያ ቤቶች እና ከሁሉም የክልል የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የተውጣጡ ባለሙያዎች በተሳተፉበት መድረክ በረቂቅ አዋጁ ድንጋጌዎች ላይ ግንቦት 13/2007 ዓ.ም፣ መስከረም 25/2008 ዓ.ም እና ሰኔ 21-22 2008 ዓ.ም ምክክሮች ተደርገዋል፡፡

በውይይቶቹም የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ልማት ኢንስትቲዩት፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ የምግብ፣የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሳይንስ ፋካልቲ (ኬሚስትሪ ዲፓርትመንት)፣ የኢትዮጵያ የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስትቲዩት፣ ከኬሚካል አምራች እና አስመጪዎች፣ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከፍትህ ሚኒስቴር እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል፡፡

### 5.1 በውይይቱ የተነሱ እና ምክክር የተደረገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

1. የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በተመለከተ የተጠቀሱት ግዴታዎችና ሃላፊነቶቾ በሙሉ አካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ለማስፈፀም የሚቸገር በመሆኑ እና አሰራር ላይ ችግር ሊፈጥር ስለሚችል ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሃላፊነት ሊውሰዱ ይገባል፡፡

በርዕሰ ጉዳዩ ላይ በተሠጠ ማብራሪያ በረቂቅ አዋጁ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን መመዝገብ እና ማስተዳደር በተመለከተ የተጠቀሱት ግዴታዎችና ሃላፊነቶቹን ለመተግበር ከፍተኛ አደረጃጀትን እና ተቋማዊ አቅምን የሚጠይቁ በመሆናቸው አዋጁን ለማስፈፀም የሚከተሉትን አማራጮች ላይ ከግንዛቤ ሊወሰዱ እንደሚገባ ተብራርቷል፡፡

- **(አማራጭ አንድ)** የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር ባለሥልጣን ወይም ኤጀንሲ በዚህ አዋጅ በማቋቋም በአዋጁ የተዘረዘሩትን ሃላፊነቶች እና ግዴታዎችን እንዲያሥፈፅም ቢደረግ፡፡
- **(አማራጭ ሁለት)** የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን የማስፈፀም ሃላፊነት ሊሠጠው ይገባል፡፡
- **(አማራጭ ሶስት)** የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአዋጁን ድንጋጌዎችን የማስፈፀም ሃላፊነት ሊውሰድ ይገባዋል፡፡

2. የኬሚካል ጉዳይ በጣም ትኩረት የሚሻና የብዙ ባለድርሻ አካላት የጋራ ስራ እና ውሳኔ የሚጠይቅ ጉዳይ በመሆኑ ይህ አዋጅ ሁሉንም የኬሚካል አይነት በበላይነት የሚቆጣጠር

መሆን አለበት ። የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ብቻ የሚመለከት መሆኑ ተገቢነቱ እንዴት ይታያል?

በዚህም ጉዳይ ላይ በተሰጠ ማብራሪያ አዋጁ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት የሚውሉ ኬሚካሎችን ብቻ የሚያካትት መሆኑን በአዋጁ ክፍል አንድ አንቀፅ 2 የኢንዱስትሪ ኬሚካል ትርጉም ስር የተገለፀ ሲሆን ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ኬሚካሎችን የማይመለከት መሆኑን ደንግጓል።

- የመድሃኒት እና የህክምና ኬሚካሎችን እና የምግብና የምግብ ነክ ኬሚካሎች ( Food and Food Additivies) (የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሀኒት ጤና ክብካቤ ቁጥጥርና አስተዳደር ባለስልጣን)
- የግብርና ኬሚካሎችን (የግብርና ሚኒስቴር)
- የኬሚካል ጦር መሳሪያዎች (ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ልማት ኢንስትቲዩት)
- ጨረር አመንጪ ኬሚካሎች (ኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለስልጣን)

ይህም የሆነበት ምክንያት በእነዚህ ዘርፎች ላይ በሀገር ደረጃ በተገቢው ሁኔታ የተዘረጋ ስርዓት እና በህግ ሃለፊነት የተሰጠው እየሠራ ያለ ተቋማዊ አደረጃጀት ያለ ሲሆን ክፍተት ያለው ከእነዚህ ውጪ በሆኑ ሌሎች የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ላይ መሆኑን ተጠቁሟል።

## 6. ማጠቃለያ

በሀገራችን እስከ አሁን ድረስ በተለያዩ ተቋማት ለተወሰኑ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን የማስተዳደር እና የመመዝገብ ተግባራት ሲከናወን ቆይቷል። ይህም ከኬሚካሎች ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመከላከል እና ለመቀነስ አዎንታዊ ሚና ተጫውቷል። በሌላ በኩል ለማምረቻ እና ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚውሉ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች መጠን እያደገ ይገኛል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ለማስተዳደር እና ለመመዝገብ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያሥችል የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ በአያያዝ ጉድለት የተነሳ በሰው፣በእንስሳት ጤና እና በአካባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል።

በመሆኑም የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አሰተዳደር አዋጅ ቢፀድቅ ከኢንዱስትሪ ኬሚካሎች አያያዝ ጉድለት በተያያዘ የሚከሰቱ የጤና ጠንቆችን ለመከላከል እና ለመቀነስ ያስችላል። በአጠቃላይም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያ እና አካባቢያው ፋይዳ ስለሚኖረው በማድግ ላይ የሚገኘውን ኢኮኖሚ ዘላቂነትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ስለዚህም የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አሰተዳደር አዋጅ የሀገሪቱን የህግ አወጣጥ ስርዓት ተከትሎ እንዲፀድቅ እንጠይቃለን።